# መቅድም

ይህ የጃቫ ጥናት ዝግጅት ነው። ዓላማው የጃቫ ቋንቋ መሰረታዊ ክፍሎችን ለማስተዋወቅና ለማስተማር ሲሆን ጥናቱ ንድፈሀሳባዊና ተግባራዊ ነው። ጥናቱ የሚሰጠው ባማርኛ ነው። ስለዚህ አንባቢውን ይረዳ ዘንድ፥ ይዘቱ በተለያየ ቅርጽ ይቀርባል።

1. በዌብ ገጽ ቋንቋ ኤች/ቲ/ኤም/ኤል (HTML) ቅርጽ፦
   ጥናቱን መስመር ላይ በዌብ መቃኛ ፕሮግራም ለማንበብ ያስችላል። አስቀድሞ በነጻ የቀረበውን የኢትዮጵያ ፊደል ፎንት ከዚህ ዌብ ገጽ ገልብጦ መቅዳት ይጠይቃል።
   http://www.senamirmir.com/download/ethiojrt.zip

2. በአዶቢ ፒ/ዲ/ኤፍ (PDF) ቅርጽ፦
   በመስመር ላይ ሆነ ወይም ውጭ፥ ፒ/ዲ/ኤፍ ጽሁፎች ለማንበብ ወይም ለማተም ይህ ቅርጽ ተመራጭነት አለው። ካንባቢው የሚጠበቀው ፒ/ዲ/ኤፍ ጽሁፎች ማንበቢያ ፕሮግራም ካዶቢ ዌብ ገጽ መገልበጥ ብቻ። http://www.adobe.com
3. በፖስትስክሪፕት ቅርጽ፦
   አንዳንድ አንባቢያን ይኸን መንገድ ይመርጡ ይሆናል። ካለይ የተጠቀሱት ሁለቱ ጐዳናዎች አጥጋቢ ካልሆኑ፥ ፖስትስክሪፕት ሌላኛው መንገድ ነው።

ዛሬ ብዙ ፕሮግራም መጻፊያ ቋንቋዎች አሉ። ጃቫ አዲስ ይሁን እንጂ ዓላማው ተመሳሳይ ነው። እንደሌሎች ሁሉ፥ የፕሮግራም መጻፊያ ቋንቋ ነው። ስለዚህ እሱን ለምን ማጥናት አስፈለገ?

1. ጃቫ፣ ባሁን ወቅት ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ ያለ አዲስ ወይም ዘመናዊ ቋንቋ ነው።ሌሎች ቋንቋዋዎች የሚሳናቸው አያሌ ጥቅሞች ይለግሳል።
2. ጃቫ የኦ/ኦ/ፕ ቋንቋ ነው። ኦ/ኦ/ፕ (Object Oriented Programming) ለችግሮች መፍትሄ ለመሻትና መፍትሄውን ረሱን በየጊዜው ለመንከባከብ ተመራጭነት ያለው መርሕ ነው።
3. የጃቫ ፕሮግራም በተገነባበት የኮምፒተር አይነት ስር ብቻ ሳይወሰን፥ ሌሎችም ዘንድ መስራት ይችላል። ይህ የጃቫ አንዱ ጠንካራ ጐን ነው።
4. የጃቫ ፕሮግራሞች ከዌብ ገጽ ጋር መዛመድ/መዋሀድ ይችላሉ። ስለሆነም የዌብ ገጾችን ግልጋሎት እጅግ ያሰፋሉ።
5. ከትንሽ ጀምሮ እስከ ግዙፍ ሶፍትዌሮች፥ በተለይ ከኢንተርነት ጋር የተያያዙ፥ ለመገንባት ጃቫ መንገዱን አጭር፥ ልፋቱን መለስተኛ፥ እንዲሁም አሰራሩን ግልጽ/ክፍት ያደረገ ቋንቋ ነው።
6. የጃቫ ቋንቋ ህጎች ከሲ++ (C++) በጣም ይቀራረባሉ። ጃቫ አብዛኛውን ነገር ያገኘው ከዛ ነው ለማለት ያስደፍራል። ለሲ++ ጸሀፊዎች ወደጃቫ ለመሻገር ወይም የጃቫ ጸሀፊዎች ወደ ሲ++ ለመዝለቅ መንገዱ አጭር ነው።

ጥናቱን ባማርኛ ማቀረብ ለምን አስፈለገ?

1. በእንግሊዘኛ የተጻፉ በብዙ ተቆጣሪ ጥናቶች፥ መጻህፎች፥ የትምህርት እድሎች በተለያየ መንገድ ይገኛሉ። በሌሎች ቋንቋዎች በኩል ግን መጠኑ ውስን ወይም ባዶ ነው። ጃቫን የመሰለ ቋንቋ ላንባቢው ተሰሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ ውጤታማ ነው።
2. ይህ ጸሀፊ ባማርኛ የተጻፈ የጃቫ ጥናት አይቶ ወይም ሰምቶ አያውቅም። ስለዚህ ጃቫ ላማርኛ አዲስ ነው። ከእንግሊዘኛ ይልቅ አማርኛ ለሚፈቅዳው አንባቢ በሩን ይከፍታል፤ በተለይ ባገር ቤት ውስጥ።
3. እንደዚህ አይነት ነገሮች ባማርኛ ቋንቋ መሞከር ከቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች፥ እድገቶች በቅርብ ለመመልከት ያግዛል የሚል ግምት በዚህ ጸሃፊ ዘንድ አለ።

ጥናቱ መሰረታዊ የሆኑትን የጃቫ ቋንቋ አካሎች ለማቅረብ ይሞክራል። ጥናቱ ባያሌ ረድፎች የተከፈለ ሆኖ፥ አንዳባንድ በየሁለት ሳምንት ይቀርባል። ባጋጣሚ ምክንያት ከዘገየ፥ ያንባቢው ግንዛቤ በትህትና ይጠበቃል።

እያንዳንዱ አብይ ነጥብ በምሳሌና በስእሎች ይደገፋል። አዲስ ቃላት ካዘለ፥ ፍቺው አብሮት ይቀርባል። ያም ሆኖ ጃቫን በያዝነው ቋንቋ ማቅረብ፥ ምንም እንኳን ስራው አጓጊ ቢሆንም፥ ቀላል አለመሆኑን አንባቢው ይረደዋል። ላሉት ስህተቶች፥ እንዲሁም ግድፈቶች ጸሀፊው ሀላፊ ስለሆነ ለሚፈጥሩት ቅሬታዎች በቅድሚያ ይቅርታ ይጠይቃል። ጥናቱ የጸሀፊውንም ሆነ ያንባቢውን ጥረት ስለሚጠይቅ፣ ለማንኛውም ትጋትና አስተያየት በሩ ክፍት ነው።

አባስ በላይ አላምነህ